# ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል -  የመልካም አስተዳደር መሠረት

ተስፋዬ ለማ

ትግራይ  ኦንላይን April 25, 2014

ብዙ የማንበብም ሆነ የመጻፍ ልምድ ባይኖረኝም አልፎ...አልፎ ጋዜጦችንና መጽሄቶችን በወፍ በረር እይታ እመለከታለሁ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን "ኢህአዴግን እናፍርሰው ወይስ እናድሰው" የሚለውን ጽሁፍ የያዘውን ዕትም አልተመለከትኩትም ነበር። አንድ ጓደኛዬ ጋር ሳወራ ጽሁፉ መውጣቱን አወጋኝና መጽሄቱን ገዝቼ አነበብኩት።

ሁለት ፀሀፊያን "እናድሰው" "እናፍርሰው" በሚሉ ሁለት ንዑሣን ርዕሶች ይዘውት የወጡት መጣጥፍ ብጤ አነበብኩና እነዚህ ሁለት ሃሳቦች የማያነጋግሩ፤ አጀንዳ ከቶ ሆነው የማይቀርቡ መሆናቸውን ተገነዘብኩ። በእኔ እምነት ሁለቱም ሃሳቦች  ቀድመው የተፈፀሙ ናቸው። ይህ ከሆነ ስለምን የመከራከሪያ አጀንዳ መሆን ቻሉ የሚል ጥያቄም በአዕምሮዬ ናኘ። ብዕር አነሳሁና ያለኝን እምነትና ሃሳብ እንደሚከተለው አሰፈርኩ።

በ "ላይፍ" መፅሄት ***"ኢህአዴግ ይታደስ ወይስ ይፍረስ?"*** በሚል ዐቢይ ርዕስ ሥር ደረጀ ፍቅሩ ደስታና ጥላሁን በቀለ ይግለጡ በቅደም ተከተላቸው ***"የለም - ኢህአዴግን እናድሰው"*** እና ***"አዎ - ኢህአዴግን እናፍርሰው"*** በሚሉ ሁለት ጫፍ የያዙ ንዑስ ርዕሶች ውስጥ ያሰፈሩትን ሃሳብ ሳነብ እውነትም አንድ ነገር ማለት እንዳለብኝ ተረዳሁ። የእኔስ እምነት በዚህ ዙሪያ ምን መሆን አለበት የሚለውን አሰላሰልኩ። እናም ውስጤን አደመጥኩና ስሜቴን ለመግለጽ ወሰንኩ።

እርግጥ ነው፤ "ኢህአዴግ"ን እናፍርሰው ወይስ እናድሰው የሚለው የመከራከሪያ ርዕስ የማያከራክር መሆኑን ተረዳሁ። በእኔ እምነት "ኢህአዴግ"ን ማፍረስም ማደስም የሚያስችል መሠረት የለም። አናፈርሰውም አናድሰውም።

እውነቱን እንነጋገር ካልን በኛ ፍላጎትና ተግባር ቢሆን ኖሮ "ኢህአዴግ"ን አፈራርሰነዋል። ካፈረስነው ቆይተናል... ደጋግመን ደጋግመን አፈራርሰነዋል። ሃያ ሦስት ዓመታት ሙሉ በደንታ ቢስነት ስንንደው  ኖረናል። ውሸት ምን ያደርጋል! "ኢህአዴግ"ን ቀድመን አፈራርሰነዋል። በ"ሰይፈ ነበልባል" አቃጥለነዋል፣ በ"ጦማር" ጨፍልቀነዋል፣ በ"ሞገድ" አንሳፍፈነዋል፣ "ነጻነት"ን እና ሌሎች በኢህአዴግ  ሥርዓት እስትንፋስ ያገኙ የአገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች ተጠቅመን በአገሪቱ ታሪክ ኢህአዴግን  ካፈራረስነው ቆይተናል።

ያከናወነውን መልካም ሥራ ሁሉ አጥቁረንበታል፣ በላዩ ላይ ሕዝብን ለማሳመፅ ያልተቆጠበ ጥረት አድርገናል፣ ያልሆነውን ሆነ፤ የሌለውን አለ እያልን አውርተናል፡፡  የውጭ ድጋፍ እንዳያገኝ ደክመናል ጥረናል፣ አገሪቱ የእለት ደራሽ የምግብ እርዳታ እንዳታገኝ ረጂዎችን ተማጥነናል፣ ያየነውን በጎ ነገር በክፋት እየመነዘርን ተናግረናል፣ ሁሉንም ነገር በተንጋደደ እይታ አይተናል፣ ሚዛናዊነት አጉድለናል፣ ከክፋታችን የተነሳም ማሩን ሳይቀር  በእሬት ለውሰነዋል።

በዚህ መልክ ኢህአዴግን ካፈረስነው ቆይተናል፤ ገና ከመምጣቱ በጨቅላ እድሜው እያለ ቀጭተነዋል። ኢትዮጵያን በታተናት፣ ህዝቧን በቋንቋ፣ በኃይማኖትና በዘር ከፋፍሎ መቋጫ

በሌለውና ሊያባራ በማይችል ቀውስ ውስጥ አስገባት ብለን ሰብከናል። ህዝብን አደናግረናል፣ ህዝቡ ኢህአዴግ ላይ እምነት እንዳያሳድር አድርገናል። በእኛ ፍላጎትና ተግባር ከሆነማ "ኢህአዴግ"ን ያኔ ድሮ አፍርሰነዋል። በእንጭጩ ቀጭተነዋል። ጉዞውን ገትተናል።

በዚሁ ብቻ ሳንቆጠብ ዳግም እንዳያንሰራራ በ1997 ዓ.ም ደጋግመን አፍርሰነዋል። ፓርቲውን ከህዝብ ለመነጠል ያልተቆጠበ ጥረት አድርገናል። አንድን ብሄር በሌላ ብሄር አነሳስተናል። ለሠላም መደፍረስ ጥረናል። ሕገ መንግሥቱ የሰጠንን ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትና መብት ኃላፊነት በጎደለው መልክ ተጠቅመንበታል። እንደኛ ቢሆን ኖሮ "ኢህአዴግ"ን ያኔ አፍርሰነዋል። በሃሰት ወንጅለነዋል፤ የያዘውን የልማት አጀንዳ አብጠልጥለናል፤ ትላልቅ አገርን የሚጠቅሙ የልማት ፕሮጀክቶችን ሳይቀር በጭፍን ተቃውመናል።
በዚህ መልክ "ኢህአዴግ"ን ካፈረስነው ቆይቷል። ኢህአዴግ ያመጣውን ለውጥ ክደናል። የአገራችንና የህዝባችንን ጥቅም አሳልፈን ከሰጠን ቆይተናል፤ ለባዕድ አገራት ፖለቲካ ማራመጃ ሆነናል፤ አንዳንዶቻችን ይባስ ብለን የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ወግነናል። ከሶማሊያና ከኤርትራ ጋር በተያያዘ የህዝባችንንና የአገራችን ጥቅም በመተው ከጠላት ጋር ወግነን ዘግበናል፣ አራግበናል ህዝብን አደናግረናል። እኛ "ኢህአዴግ"ን ካፈረስነው የቆየን ስለሆነ ስለማፍረስ የምንነጋገርበት ወቅት አልፏል፤ ነፍሶበታል።

"አዎ - ኢህአዴግን እናፈርሰዋለን" በሚል ንዑስ ርዕስ ሃሳቡን የሰነዘረው ወዳጄ ጥላሁን በቀለ ካነሳቸው ነጥቦች አንዱ "ኢህአዴግ"ን የሚያስመሰግኑ በርካታ የልማት ተግባራት ማከናወኑን ይገልጻል። የእነዚህ በርካታ ለውጦች መቋጫ 'መልካም አስተዳደርን' ማስፈን በመሆኑ ይህንን ማድረግ ባለመቻሉ እናፍርሰው" ይላል።

የመልካም አስተዳደር እጦት ከምን ይመነጫል? ኪራይ ሰብሳቢነትንና የመልካም አስተዳደር እጦትን ለማስወገድ መሠረታዊው ነገር ምንድን ነው? የሚለውን ማየት ጠቃሚ ይሆናል። ሁለቱም በዋናነት የሚመነጩት ከአስተሳብ ነው። አስተሳሰብን መቀየር በመሠረታዊነት መልካም አስተዳደርን ማስፈን ነው።

ኪራይ ሰብሳቢነትን ማዳከምና ልማታዊ ልዕልናን ማረጋገጥ እንደሆነ እሙን ነው። የሰውን ልጅ አስተሳሰብ መቀየር ደግሞ ረዥም ጊዜ የሚሻ ነገር ነው። በተለይ እንደ አገራችን በመሳሰሉ በኋላ ቀር አስተሳሰብና በፊላጭ ቆራጭ ሥርዓት ያለፉ ህዝቦችን አስተሳሰብ መቀየር ከፍተኛ ጥረትን ይጠይቃል።

አስተሳሰብ ሲባል የፖለቲካ ጨዋታ የሚመስላቸው በርካቶች አሉ። ከዚህ ጋር የተያያዘ በሌሎች የዓለማችን አገራት ያለው ሁኔታ ግን በጣም የተለየ ነው። ለአብነት ያህል በሆላንድ አገር የትምህርት እድል አግኝቶ ለአራት ዓመታት በዚያ አገር የኖረ አንድ ጓደኛዬ ያጫወተኝን ነገር ላውጋችሁ።

የማነሳው ምናልባትም አስተሳሰብን መለወጥ የሚለውን ነገር ለማብራራት ያግዝ ይሆናል በሚል እምነት ነው። በሆላንድ አገር በነበረው ቆይታ ዘመድ ለመጠየቅ የሚማርበት ዩኒቨርስቲ ከሚገኝበት ከተማ ተነስቶ ራቅ ወዳለ አንዲት ዘመዱ ወደምትኖርበት ከተማ በየሣምንቱ በባቡር ይመላለስ ነበር። በተደጋጋሚ ስለሚመላለስ በየጊዜው የባቡር ትኬትን ይቆርጣል።

በተለይ ለቅዳሜና እሁድ የሚሆን ትኬት የሚቆረጠው አርብ ቀን በመሆኑና ይህ ትኬት በየአካባቢው ከተተከለ ማሽን ስለሚቆረጥ በየሣምንቱ መልሰህ መላልሰህ መጠቀም የሚቻልበት

ኢጋጣሚ አለ። አንድ ጊዜ ቆርጬ ለምን ለበርካታ ጊዜ አልጠቀምበትም የሚል ሃሳብ ትኬቱን በቆረጠ ቁጥር ወደ አዕምሮው ይመላለስ ነበር።

ለዚህ መነሻው ደግሞ ባቡር ስትሳፈር ትኬት ይኑርህ አይኑርህ የሚጠይቅ ሰው የለም። ቆረጥክ አልቆረጥክ የሚያረጋግጥ ሰው የለም። ትኬት ባለመያዝህ ውረድ የሚል ትኬት በመያዝህ ተሳፈር የሚል ሰው የለም። ይህንን የሚሰራ ሰው ባለመኖሩ የተነሳ አንድ ጊዜ በቆረጥከው ትኬት ብዙ ጊዜ ብትጠቀም ባትጠቀም የሚከታተልህ የለም። እናም ያ ኢትዮጵያዊ  በአንድ ትኬት ደጋግሞ ለመጠቀም ሁሌ ያስብ ነበር።

ሆላንዳዊያኑ ግን ሁሉ ጊዜ ትኬቱ ይቆርጣሉ። እንድ ጊዜ እንደተጠቀሙ ይጥሉታል። ምንም ዓይነት ማጭበርበር አይታይባቸውም። ሁሉንም ነገር ራሳቸው ያደርጉታል። አገልግሎት ያገኛሉ፤ ለሚያገኙት አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ በራሳቸው ይፈጽማሉ። በየዕለቱ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ። ተሳስቶ ትኬት ሳይቆርጥ የሚሳፈር አንድም ዜጋ  እንደሌለ ያስተውላል።

ትኬት ቆርጠው ይሳፈሩ ያለ ትኬት ይሳፈሩ የሚጠይቅ ሰው የለም። ሁሉንም ነገር በራሳቸው ያደርጉታል። ያ ወዳጄ በሆላንዳዊያኑ ተግባርና ድርጊት እንዲሁም  ለራሳቸው ባላቸው ታማኝነት ተገርሞ ለምን እንደሆነ ከራሳቸው ጠይቆ ለመረዳት ይወስናል።
አንድ ቀን አጠገቡ ተቀምጣ ትጓዝ የነበረችን ወጣት ይህንን ጉዳይ ይጠይቃታል። "እናንተ በየቀኑ ስትመላለሱ ትኬት ትቆርጣለችሁ፣ መቁረጥና አለመቁረጣችሁን የሚያይና የሚያረጋግጥ ሰው የለም፤ ስትሳፈር ትኬት መያዝህን የሚያይ የለም። ማንኛውም ሰው ምንጊዜም ትኬት ሳይዝ ወደ ባቡሩ ሲገባ አይታይም። ይህ እንዴት ሆነ? የሚል ነበር ጥያቄው። ወጣቷም መለሰች "እስኪ ወደ ኋላ ተመልከት ምን ያህል ተጓዥ አለ? ስትል መልሳ ጠየቀችው። መልሱን ሳትጠብቅም የነበረው ሰው አነስተኛ ነበርና "አየህ" አለች ወጣቷ "ይህ ባቡር የኔ ነው። እኔን ለማድረስ ነው ይህንን ያህል አነስተኛ ቁጥር ያለው ተጓዥ ይዞ ይህን ያህል ረዥም መንገድ የሚጓዘው።" "እኛ ከምንቆርጠው ትኬት የሚሰበሰበው ገንዘብ ነዳጅን የሚሸፍን አይደለም። ስለዚህ ለምን በዝቅተኛ ክፍያ የሚያመላልሰንን የራሳችን የሆነ ባቡርን ሂሳብ እናጭበረብራለ?።"  ነበር ያለችው። ይህ አስተሳሰብ የበለፀገ አስተሳሰብ ነው።

በባህላቸው ሌብነትን አስወግደዋል። ሕግን የሚያከብሩት ተቆጣጣሪን በማየት ሳይሆን ለራሳቸው በመታመን ብቻ ነው። ለነገሩ ለራሱ ያልታመነ ለማን ሊታመን ይችላል? እንደዚህ ዓይነቱ ነገር ከባለቤትነት ስሜት መዳበር ጋር አብሮ የሚመጣ ነው። የአስተሳሰብ ለውጥ የሚባለውም ይኼ ነው። መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማስወገድ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ቀዳሚው ተግባር ነው። ይህንን ማድረግ ከተቻለ ብቻ መልካም አስተዳደር ይሰፍናል፣ ኪራይ ሰብሳቢነት ይወገዳል።

ሌላው ደግሞ የመልካም አስተዳደር መስፈን ከልማት ተጠቃሚነት ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው። ድህነት ባለበትና ህዝቡ ከአገሪቱ ሃብት በየደረጃው ተጠቃሚ ባልሆነበት ሁኔታ መልካም አስተዳደርን በዘላቂነት ማስፈን አይቻልም። ለዚህም ነው ኢህአዴግ ልማትን ማፋጠንና የህዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ዋና አጀንዳው አድርጎ እየሰራ ያለው።

ለመልካም አስተዳደር መስፈን ህዝቡ የሚኖረው ድርሻ የጎላ ነው። በዚህ ረገድ ህዝብን ለማነቃነቅ እየተሰራ ያለው ተግባርም በአጭር ጊዜ የሚበረታታ ውጤት ማምጣት ባይችልም በሂደት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል አቅጣጫ እንደሆነ የሚካድ አይደለም። ቀደም ሲል በአገራችን የነበረው ሁኔታ ሲታይ ሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩል ተጠቃሚ

አልነበሩም። አሁን ባለው ሥርዓት ግን የመንገድ፣ የመብራት፣ የውኃ፣ የትምህርት፣ የጤና ተጠቃሚ እየሆነ ያለው ኅብረተሰብ ምን ያህል እንደሆነ መገንዘብ ብቻ ኢህአዴግ ምን ያህል የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት እየሰራ እንዳለ ያሳያል።

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችሉ መሠረቶች እያበጀ የመጣው ኢህአዴግ በቀጣይ ዋና አጀንዳው አድርጎ እየሰራበት በመሆኑ እንደሌሎች ውጤታማ ተግባራቱ በዚህ ረገድም ስኬታማ እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይደለም። ስለዚህ ልማትን አምጥቷል፣ በርካታ ለውጦችን እውን አድርጓል፤ ነገር ግን መልካም አስተዳደርን ማስፈን ባለመቻሉ እናፍርሰው የሚለው ሃሳብ እርስ በርሱ የተጣረሰ ነው።

ልማትን ማምጣትና ለውጥን ማስመዝገብ ድህነትን ለማስወገድ ብቸኛ መፍትሄ ሲሆን ድህነትን ማስወገድና የአገሪቱን ህዝብ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን እድገት ማምጣት ለመልካም አስተዳደር መስፈን የጎላ ድርሻ ስላላቸው ይህንኑ እውን ማድረግ በሚያስችል ትክክለኛ ጎዳና ላይ የሚገኘውን ኢህአዴግን እናፍርሰው ለማለት የሚያስችል አስረጂ ያልቀረበበት ለማለት ብቻ የተባለ እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም።

በተቃራኒው የተነሳው "ኢህአዴግ"ን አናድሰውም የሚለውም ሃሳብ በእኔ እምነት ትክክል ነው አልልም። በእውነቱ ከሆነ እኛ "ኢህአዴግ"ን አናድሰውም። ኢህአዴግ በጽናቱና በጥረቱ ሕዝብ ሆኗል፤ በህዝብ መንፈስ ሰርጿል። በሰማዕታቱ አጥንት፣ በሰማዕታቱ ቃል ኪዳን ራሱን አጽንቷል። ምንጊዜም ራሱን እየፈተሸ ከስህተቱ እየተማረ ራሱን የሚያድስ ድርጅት ሆኗል።

በመሆኑም እኛ ልናድሰው ሥነ ምግባራዊ፣ ሥነ ሙያዊና ሥነ ልቦናዊ ብቃት አይኖረንም። ያለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የሚያሳዩት እኛ "ኢህአዴግ"ን ስናፈርስ "ኢህአዴግ" ልማትን ሲገነባና ራሱን ሲያድስ መኖሩን ነው። እኛ ስናፈርስና ስናጣምም ኢህአዴግ ሲገነባና ሲያቃና ሃያ ሦስት ዓመታት ተቆጥረዋል። ከዚህ መነሻ "እህአዴግ" ን አናድሰውም። ይሁንና ኢህአዴግ ራሱን በሰማዕታቱ መስዋዕትነትና በጽናቱ የታደሰ ቢሆንም እኛም እናድሰው ብንል ምን ክፋት አለበት? የሚባል ከሆነም ለማደስ የሚያበቃው አስረጂ በተገቢው መንገድ ማቅረብ ይጠይቃል።

ራሱን እያደሰ የመጣውን ኢህአዴግ፣ በህዝብ እየታደሰ የመጣውን ኢህአዴግ ራሱን አብቅቷልና ሕዝቡም ተቀብሎታልና፣ እያከናወናቸው ያሉ ልማታዊ ተግባራት እንዲታደስ አድርገውታልና እኛም ይሁንታ መስጠት አለብን በሚል እምነት ከተነሳሳን ደግሞ ምክንያታችን በጽሁፉ የቀረበው ዓይነት እንዳልሆነ መገንዘብ የግድ ነው። አበው ሲተርቱ "ለመሸበት እንጨትም ይሸብታል" ይላሉ። እንጨትም በጊዜው መሸበቱ የግድ ነው። የአርባ ዓመታት ጎልማሳ በመሆኑ ምክንያት "ኢህአዴግ"ን እናድሰው ማለት ተገቢነት የለውም።

እርግጥ ነው፤ ኢህአዴግ አገሪቱን አድሷል፣ የህዝቡ የሥራ ባህል ተቀይሯል፤ የህዝቦችን እኩልነት አረጋግጧል፤ በዚች አገር ወዳጅ ብቻ ሳይሆን ጠላት የሚመሰክርለት ለውጥንና እድገትን አምጥቷል፣ በውስጥና በውጭ በየጊዜው ያገጠሙትን ፈታኝ ነገሮች ተቋቁሞ አገሪቱን በህዳሴ ጎዳና እያራመዳት ይገኛል፤

ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ባሳየው ተጨባጭ ለውጥ ራሱን አድሷል። እኛም ቢሆን በተጠቀሱት ምክንያቶች እናድሰው የሚለው ምናልባት ያግባባን ይሆናል። "ኢህአዴግን እናድሰው" በሚለው ንዑስ ርዕስ የቀረበው ሌላው ሃሳብ ደግሞ "መንግሥት ደርግን ደመሰስኩ፣ መንገድ ሰራሁ፣ ግድብ ገነባሁ ማለቱን ካቆመ መታደስ አለበት" ይላል። ይህ ማለት ምን ማለት ነው?

ኢህአዴግ የሚሰራውን ሥራ ወደ ህዝብ ሳያወርድ ከህዝብ ጋር ሳይወያይ፣ ህዝብን ሳያሳምን፣ የህዝብን ይሁንታና ድጋፍ ሳያገኝ በምስጢር ይስራ ማለት ነው? የህዝብ ልማት፣ በህዝብ ባለቤትነት የሚመራ ነው። በመሆኑም የሚሰራውን አጠቃላይ ሥራ ለሚፈጽመው ህዝብ ማሳወቅ ክፋቱ ምን ላይ ነው? ምናልባት ክፋት የሚሆነው አረዳዱ ላይ ብቻ ይመስለኛል።

በአገሪቱ እየተከናወነ ያለው ልማት ባለቤት የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ለዚህ ልማት መሳካት የህዝብ ተሳትፎ ወሣኝ ነው። ተሳትፎ የሚጠናከረው ደግሞ ጠቀሜታውንና ዓላማውን በአግባቡ ማስገንዘብ ሲቻል እንደሆነ እሙን ነው። አገሪቱ ቀደም ሲል የነበራትን የድህነት፣ የጦርነትና የረሃብ ገጽታ በአሁኑ ወቅት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በማሳየት ህዝቡን ለበለጠ ለውጥና ለላቀ ስኬት መቀስቀስ ምን ክፋት አለው? ክፋቱ በቅንነት መረዳት አለመቻሉ ብቻ ይሆናል ብዬ አምናለሁ። በመሆኑም የቀረበውን ሃሳብ በውል ላጤነው የሚሰጠው ትርጉም ኢህአዴግ ልማትን ያቁምና እናድሰዋለን የሚል እምነት የሚያንፀባርቅ ሃሳብ ነው። ይህ ደግሞ የአገሪቱንና የሕዝቦቿን ነባራዊ ሁኔታን ያላገናዘበ በመሆኑ አሳማኝ ነው ብዬ አልገምትም።

ይሁን እንኳን ቢባል የቀረበው ምክንያት ለኢህአዴግ መታደስ ደካማ እንጂ በቂ ምክንያት አይደለም። ደጋም ነፈሰ ቆላ "ኢህአዴግ" በተጨባጭ ተግባሩ ታድሷል። በሕዝብ መንፈስ ሰርጾ ሕዝባዊነቱን በማስመስከር ራሱን በራሱ አድሷል። እኛ አናድሰውም። በቀጣይም በተጨባጭ ተግባሩ እየታደሰ ይሄዳል። እኛ ላለፉት ሃያ ሦስት ዓመታት ኢህአዴግን አፍርሰናል...ኢህአዴግ በጽናቱ እየታደሰ ዘልቋል።
አሁን ኢህአዴግን ማፍረስም ሆነ ማደስ ከአቅማችን ሸቅብ ወጥቷል። ሕዝብን ይዞ ከእኛ መዳረሻ ተሻግሯል።

በመሆኑም "ኢህአዴግ"ን ማደስም ማፍረስም የምንችልበት መሠረት ተንዷል። እስካሁን እንዳደረግነው ሁሉን ነገር በጥላቻ እየፈረጅን በጭፍን አተያይና በተንጋደደ አስተሳሰብ እየተነተን ጩኸታችንን ልንቀጥል እንችል ይሆናል። "ኢህአዴግ"ን ግን ከቶ አናፈርሰውም፤...ከቶም አናድሰውም፤ በእኛ ተግባር ፈራርሷል በሰማዕታቱ መስዋዕትነትና ቃል ኪዳን በሕዝብ ይሁንታ በጽኑ መሠረት ላይ ቆሟል። ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍልን እውን እያደረገ ይገኛል። መብራት፣ ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ ትምህርትና ህክምና አይተው የማያውቁ ህዝቦች በአሁኑ ወቅት የአገራቸው ሃብት እኩል ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል። ይህ ነው የመልካም አስተዳደር መሠረት ማለት።